6-1-01/230/10

በኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን
ለከፍተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት
ለምስራቅ መካከለኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ት
ለምዕራብ መካከለኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት
ለአዳማ ቅ/ጽ/ቤት
ለባህር ዳር ቅ/ጽ/ቤት
ለድሬደዋ ቅ/ጽ/ቤት
ለመቀሌ ቅ/ጽ/ቤት
ለኮምቦልቻ ቅ/ጽ/ቤት
ለሐዋሳ ቅ/ጽ/ቤት
ለጅማ ቅ/ጽ/ቤት

በያሉበት

የኢትዮጵያ የሂሳብ አያያዝና ኦዲት ቦርድ በአዋጅ ቁጥር 847/2006 አንቀጽ 8/1 እና 4/2/ሸ መሠረት ማንኛውም ሪፖርት አቅራቢ አካል ቦርዱ በሚያወጣው የጊዜ ሰሌዳ መሠረት የሂሳብና የኦዲት ሪፖርቱን ለቦርዱ ማቅረብ እንዳለበት እንዲሁም በአዋጁ አንቀጽ 8/3 መሠረት ሪፖርት አቅራቢ አካላት ለሴክተሮች ሥልጣን ለተሰጣቸው የመንግስት መ/ቤቶች የሚያቀርቡት ሪፖርት ለቦርዱ የቀረበው የሂሳብ ሪፖርት ኦሪጂናል ቅጂ መሆኑን መነሻ በማድረግ ሪፖርት አቅራቢ አካላት እንዲመዘገቡና ሪፖርታቸውን ፋይል እንዲያደርጉ ቦርዱ የተለያዩ ጥሪቶች ቢደdረግም በተቀመጠው የጊዜ ሰሌዳ መሰረት የተመዘገቡና ሪፖርት ያቀረቡ ተቋማት ቁጥር አነስተኛ መሆኑን በመግለጽ ማንኛውም ግብር ከፋይ ኩባንያ እንዲሁም እመታዊ የሽያጭ ገቢያቸው ከብር 1 ሚሊዮን በላይ የሆኑ ግብር ከፋዮች በቦርድ እንዲመዘገቡና ሪፖርታቸውን እንዲያቀርቡ እንደመስፈርት ተይዞ መልዕክት እንዲተላለፍላቸው በቁጥር ኢሂአቦ/1239/09 በ09/01/2010 ዓ.ም ጠይቋል፡፡

በዚሁ መሰረት ማንኛውም ግብር ከፋይ ድርጅትና ዓመታዊ ገቢያቸው ከብር 1,000,000 /አንድ ሚሊዮን/ በላይ የሆኑ ግብር ከፋዮች የሚያቀርቡት የሂሳብ መግለጫ ለቦርዱ የቀረበው ኦርጂናል ቅጂ መሆኑ እየተረጋጠ እንዲቀርብ በቅ/ጽ/ቤታችሁ ለሚስተናገዱ አካላት ማሳሰቢያ እንዲሰጥና ተፈጻሚ እንዲደረግ እናስታውቃለን፡፡

ከሠላምታ ጋር

ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን
ታፈለ ዝማርያም
የአገር ውስጥ ታክስ ቅ/ጽ/ቤቶች
ጉምሩክ ድጋፍ ዳይሬክቶሬት
ዳይሬክተር

ግልባጭ፡-

- ✓ ለፌዴራል አገር ውስጥ ታክስ ፕሮግራም ልማትና ድጋፍ ስራዎች ዘርፍ
- ✓ ለአዲስ አበባ ታክስ ፕሮግራም ልማትና ድጋፍ ሥራዎች ዘርፍ
- ✓ ለደንበኞች አገልግሎት ዳይሬክቶሬት

የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን

- ✓ ለኢትዮጵያ የሂሳብ አያያዝና ኦዲት ቦርድ

አዲስ አበባ

10.1.0.50/0ሠ